በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# የኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# መታወቂያ ምልክቶች


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መስከረም ፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ መታወቂያ ምልክቶች

**ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ማለት ምን ማለት ነው?**

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ ለፊልሞና… በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን፡፡›› ***ፊል 1-2፡፡*** በማለት እንደተናገረው ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ታናሽ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ተጋቢዎችና ልጆቻቸው በእግዚአብሔር አማካይነት ተቀራርበው በዙሪያቸው ላሉ ሁሉ ብርሃናቸውን የሚያበሩበት አካል ነው፡፡

***የቤተሰባዊ ፍቅር ቁልፍ ነገሮች***

1. **በጋራ የሚጸልዩበት የጸሎት ቦታ**

- ቤተሰቡ አብሮ የሚጸልይበት፣ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብበትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመንፈሳዊ ሕይወት በመተሳሰር የሰይጣንን ፈተና ሁሉ ድል የሚነሳበት አብሮ የሚጸልይበት ቦታ አለው፡፡ *1ኛ ተሰ 5፡17፡፡*

2. **ቅዱስ ቁርባንን አብሮ መቀበል**

- ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹እግሮቼ በቅንነት ቆመዋልና አቤቱ፥ በማኅበር አመሰግንሃለሁ፡፡›› መዝ **25(26)፡12** እንዳለ ቤተሰቡ ንስሐ ገብቶ ቀኖናውን ፈጽሞ አብሮ ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ኦርቶዶክሳዊ ማንነቱን ይገልጣል፡፡

3. **ችግሮቻቸውን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ**

- ልጆች ችግር ሲገጥማቸው እጃቸውን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት እንዲያነሱ ማስተማር ታላቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ እግዚአብሔር በችግሮቻችን መካከል ጣልቃ ገብቶ እንዲፈታልን የሚያደርገው ይህ አካሄድ ነውና፡፡ ‹‹በመከራ ቀን ጥራኝ፥ አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ፡፡›› ***መዝ 49(50)፡15፡፡***

# የኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ መታወቂያ ምልክቶች

4. በነገሮች ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝ

- በሥራ ብዛት የተያዘ አባት፣ ሥራ ውላ በምትገባ ሚስትና የተለያዩ ችግሮችና ግጭቶች የሚገጥሟቸው ልጆች ባሉበት በዚህ ዘመን ስለዛሬውም ሆነ ስለወደፊቱ ባላቸው ሐሳብ ወይም ስጋት ቢከራከሩም በመንፋሳዊ መግባባት ማጠናቀቅና የጋራ መንፈሳዊ አቋም መያዝም ያስፈልጋቸዋል፡፡
- በራስ ወዳድነት ችግርን ለችግሩ ባለቤት ብቻ ትቶ እግርን አጣጥፎ መቀመጥ ታላቅ ወንጀል ወይም በደል ነው፡፡ ስለዚህ የራሳችንን የራስ ወዳድነት መንገድ ትተን ለሌሎች ጠቃሚ በሆኑ የጋራ መንገዶች መገኘት ይጠበቅብናል፡፡

5. እርስ በርስ መጠያየቅ

- ኦርቶዶክሳዊ (ክርስቲያናዊ) አንድነታችንንና ፍቅራችንን ያጠነክርልን ዘንድ እርስ በርስ መጠያየቅ መልካም ነው፡፡
- ስለዚህ በጎረቤታችን ያሉ፣ ከከተማችን ርቀው የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን በዓላትን ወይም ሌሎች አጋጣሚዎችን በመፍጠር መጠየቅ ይገባል፡፡
- ሚስት ለባልዋ ባልም ለሚስት ቤተሰቦች ፍላጎች ወይም ስሜት ትኩረት/ክብካቤ ማድረጋቸው አስፈላጊ ነው፡፡ በርካታ ችግሮች የሚፈጠሩት እነዚህን ጉዳዮች በመዘንጋት ነው፡፡
- የሁለቱ ወገን ቤተሰቦች መተሳሰር ለኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ታላቅ ኃይል የሚሆን ሲሆን ሥነ ልቦናቸው የተስተካከሉ ልጆችንም ለማሳደግ ታላቅ መሠረት ነው፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ መታወቂያ ምልክቶች

6. ሰላም ደስታ የሚገኝበት ክፋት የማይታይበት መንፈስ

- ቤተሰብን የሚያበላሸው ታላቁ ነገር ከለላው ቤተሰብ የሚገጥም አስመሳይነትና ክፋት ነው፡፡ እግዚአብሔር በረድኤቱ የጠበቃት በመንፈሳዊነት ያበለጸጋት የክርስቲያኖች ነፍስ ግን በሰማያዊ ሰላም ተሞልታ ‹‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም፡፡›› ***መዝ 22(23)፡1፡፡*** በማለት ትዘምራለች፡፡
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ትሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፥አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል፡፡ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያስንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 6፡6-9፡፡*** በማለት በሰጠው ምክር ሁሉም ራሳቸውን መገምገማቸው እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

7. ልጆችን በሥርዓት ማሳደግ

- ወላጆች ልጆቻቸውን በየዕድሜ ክልላቸው እየተከታተሉ ማሳደጋቸው እጅግ ተገቢ ነው፡፡ በየመሐሉ ጣልቃ እየገቡ አንዳንዱ መቆጣት አንዳንዴም ችላ ማለት ልጆቹን ግራ በመጋባት እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል፡፡ በልጆች መካከልም የማይመሳሰል ወጣ ገባ አካሄድን መከተልም ልጆችን ለታላቅ ግራ ተጋብቶ የማደግ አደጋ ያጋልጣቸዋል፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ መታወቂያ ምልክቶች

7. ልጆችን በሥርዓት ማሳደግ…

- ጤናማ የሆነው ኦርቶዶክሳዊ አቀራረብ በግልጽነት መወያየትን በፍቅር ማቅረብን የምንግልጽበት ሲሆን ያላግባብ አስፈላጊ ባልሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ጣልቃ ገብነትን የማይጋብዝ ነው፡፡
- ይሁን እንጂ በክርስትናችን እሴቶች አስተምህሮዎች ቸልተኛ ሆነን ልጆቻችን እንዲጠፉ ምክንያት ከመሆን መጠንቀቅም ያስፈልጋል፡፡
- በልጆቻቸው ጉዳይ ከሌላ ቤተሰብ ጋር መነጋገርን የሚጋብዝ ነገር ሲፈጠር ወላጆች በንቃት ተሳትፈው ወደ ጤናማ አቅጣጫ ልጆቻቸውን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዴት መነጋገር እንዳለባቸው የሚጠቁሙ አቅጣጫዎች ሊኖሩአቸው ያስፈልጋል፡፡
- በተመጣጠነ ሁኔታ ካደጉ መልካም ጓደኛ መምረጥ የሚያስችላቸው አቅም ይገነባሉና ወላጆች ልጆቻቸውን በርኅራኄና በመረዳት መከታተልም ይጠበቅባቸዋል፡፡

8. ቤተሰብና ማኅበረሰቡ

- አንዳንድ ጊዜ ወላጆች ለልጆቻቸው ግድየለሽ ሆነው በዙሪያቸው ለሚገጥማቸው የወጣትነት ጫና እንዲጋለጡ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ልጆቹም በዚህም በመራመድ ራሳቸውን ወደ ችግር ይከታሉ፡፡
- ትክክለኛው ኦርቶዶክሳዊ መንገድ በየጉዳዩ በፍቅርና በማገዝ መንፈስ መቅረብን የሚሻ ሲሆን ለሃይማኖታዊ እሴቶችና አስተምህሮዎች ግድየለሽነት አሳይተን ለአደጋ እንዳናጋልጣቸው መጠንቀቅንም ይፈልጋል፡፡
- ወላጆች ከሌላ ቤተሰብ ጋር የሚደረጉ ግኑኝነቶችን እንደ ጉዳያቸው በመመልከት ተሳትፎ በማድረግ ወደ ተገቢ አቅጣጫ ልጆቻቸው እንዲመሩ ያስፈልጋል፡፡
- መገደብ በሚገባው ቦታ ያልተገደበ የዋህ ወዳጅነት አደገኛ ችግሮችን የሚያስከትልባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ስለሆኑ ዘወትር ጥንቃቄ ሊከበን ይገባል፡፡

# የኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ መታወቂያ ምልክቶች

9. **ቤተሰብና መገናኛ ብዙኃን**

- በቤታችን ቲቪ፣ ሬድዮ፣ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችን ማንበባችን ኃጢአት አይደለም፡፡ ነገር ግን ልጆችም ሆኑ ወላጆች ትክክለኛውን ነገር እንዲመርጡ አለማድረግ ግን ታላቅ ጥፋት ነው፡፡
- ሁሉም አእምሮአቸውን ሊገነባ የሚችለውን መርሐ ግብሮ፣ ጠቃሚ መጻሕፍቶች ወዘተ መምረጥ የሚያስችል መንገድ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡
- እንዲሁ ደግሞ ጠቃሚ ካሎሆኑ ነገሮች ልጆቻችንን ልንጠብቅ መቻል አለመቻላችንን ማረጋገጥና ምንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሊያጠፋ ከሚችል ጥፋት መታደግ ይገባናል፡፡
- ንጹሕ የሆነውን የክርስትና ትምህርት ፍቅርን የሚገነቡ ኦርቶዶክሳዊ የሃይማኖት ዕውቀታችንን የሚያሰፉ ምንጮች ጠቃሚ ስለሆኑ ልንጠቀምባቸው የሚገቡ ሲሆኑ ለዚህ ተቃራኒ ከሆኑትም ተሰቡ ሊርቅና ሊቆጠብ ይገባል፡፡

7. **ሌሎችን ማገልገል**

- ጌታችን ‹‹የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፡፡›› *ማቴ 20፡28፡፡* በማለት እንደነገረን ማገልገል የኦርቶዶክሳውያን አንዱ ምልክት ነው፡፡ ልጆቻችንን ራስ ወዳድነትን ካስተማርናቸው ዘመዶቻቸውን ሳይቀር ጠልተው ጥቅማቸውን ብቻ የሚያሳድዱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለማስተካከልም ታላቅ ዋጋ ያስከፍሉናል፡፡
- ‹‹ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል፡፡›› *ቀዳ ቆሮ 13፡4-7፡፡* እንደተጻፈልን ክርስትና ራስን መሥዋዕት ማድረግን ይሻልና ጊዜያችንን፣ ገንዘባችንን፣ ጉልበታችንንና ችሎታችንን ሁሉ ከሁሉ ይልቅ በቤተክርስቲያን ውስጥ በማቅረብ ሌሎችን እናገልግል፡፡
- አሥራታችንንም ለመክፈል ታማኞች እንሁን ‹‹በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ…›› *ሚል 3፡8-11፡፡*

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org